*መልእክት አሥራ አንድ*

# የዕዝራ አገልግሎት እና የነህምያ አመራር ውስጠ-መሠረታዊ ትርጉም— አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን በመኖር እና በመሥራት እንደ እግዚአብሔር ቤት እና እንደ እግዚአብሔር መንግሥት ቤተ ክርስቲያንን መገንባት

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ራእ. 21፡:2፣ 9-11፣ 18፣ 22፡1

**I. የዕዝራ አገልግሎት ውስጠ-መሠረታዊ ትርጉም *መንጻት፣ ትምህርት እና መልሶ-ማቀናበር* በሚሉት ቃላት ውስጥ የተካተተ ነው፤ የነህምያ አመራር ውስጠ-መሠረታዊ ትርጉም *መለየት፣ ጥበቃ እና መገለጥ* በሚሉት ቃላት ውስጥ የተካተተ ነው፤ በዚህ ውስጠ-መሠረታዊ ትርጉም መሠረት አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን በመኖር እና በመሥራት ቤተ ክርስቲያንን እንደ እግዚአብሔር ቤት እና እንደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመገንባት በሰማያዊው አገልግሎቱ ከጌታ ጋር መተባበር ያስፈልገናል—1 ነገ. 8፡48፤ መዝ. 48፡1-2፤ 1 ጢሞ. 3፡15፤ ኤፌ. 2፡21-22።**

**II. በዘመኑ አገልግሎት ውስጥ በዘመኑ ራእይ መሠረት እግዚአብሔርን መኖር እና ማገልገል አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን መኖር እና መሥራት ነው፡- “ ቅጥርዋም ከኢያሰጲድ የተሠራ ነበረ፥ ከተማይቱም ጥሩ ብርጭቆ የሚመስል ጥሩ ወርቅ ነበረች”— ራእ. 21፡18፤ ሐዋ. 26፡19፤ 22፡15፤ ራእ. 21፡2፣ 9-11፡-**

ሀ. ከተማይቱ እንደ የጠራ ብርጭቆ ንጹሕ ወርቅ መሆኗ፣ በቅዱስ ባሕሪው በእግዚአብሔር *መንጻት* እንደሚያስፈልገን እና የእግዚአብሔርን ኃሳቦች እና መንገዶች ግልጽ እንዲያደርግልን ለአእምሮአችን መታደስ እና አብርሆት ማግኘት የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርቶች በአእምሮአችን ላይ በመተግበር *በመማር* አማካኝነት አብርሆት ማግኘት እንደሚያስፈልገን ያመለክታል—ተዛ. ማቴ. 5፡8፤ ኤፌ. 4፡23፤ ዮሐ. 17፡17።

ለ. በሦስታንዱ አምላክ መልሰን እንገነባ ዘንድ እና ሌሎችን በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ውስጥ ያሉ ማንነቶች ያደርጋቸው ዘንድ ራሱን ወደ ሌሎች ማንነት ውስጥ ለመገንባት እርሱን ወደ ሌሎች ውስጥ እናገለግለው ዘንድ “የግንባታው *ሥራ*” በእርሱ *መልሶ-ለመቀናበራችን* ልዩና ብቸኛው የእግዚአብሔር *ሥራ* ነው—1 ቆሮ. 3፡9፣ 12፤ ኤፌ. 3፡16-19፤ ራእ. 3፡12፤ መኃ. 6፡4፤ ዕብ. 11፡10።

ሐ. ለእግዚአብሔር ሕዝብ *መለየት* እና ለእግዚአብሔር ፍላጎት *መጠበቅ፣* ከተማይቱ ከቅጥርዋ ጋር፣ በእግዚአብሔር ራስነት ሥር እንደ ዘላለማዊው የእግዚአብሔር መንግሥት አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን ታመለክታለች—ነህ. 4፡17፤ ኤፌ. 5፡26።

መ. የከተማይቱ ቅጥር ኢያሰጲድ (የእግዚአብሔር ሕይወት በብልጥግናው) መሆኑ እና ከተማይቱ ወርቅ (የእግዚአብሔር መለኮታዊ ባሕሪይ) መሆኗ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ለልዩና-ብቸኛው *መገለጡ* በሕይወት እና በባሕሪይ ተመላኪነቱን ሳይጨምር እኛን ከእርሱ ጋር አንድ ዓይነት ለማድረግ መሆኑን ይገልጣሉ—ዘፍ. 1፡26፤ ዮሐ. 10፡10፤ 2 ጴጥ. 1፤4፤ ራእ. 4፡3፤ 21፡10-11፣ 18።

**III. አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን መኖር እና መሥራት በዕዝራ አገልግሎት እና በነህምያ አመራር ውስጠ-መሠረታዊ ትርጉም ውስጥ መኖር እና ማገልገል ነው፡-**

ሀ. ጌታን እና የዘላለማዊ ኢኮኖሚውን ፍላጎቶች እንደ ልዩና ብቸኛ ግባችን በመውሰድ ከድብልቆች ሁሉ በመንጻት ሂደት ውስጥ መቆየት ያስፈልገናል—ዕዝ. 9፡2፤ ማቴ. 5፡8፤ 1 ጢሞ. 3፡9፤ 2 ቆሮ. 6፡4፣ 6፤ ሉቃ. 9፡54-55፤ ዕብ. 4፡12፤ 1 ነገ. 8፡48፡-

1. በእግዚአብሔር አብርሆት የመስጠት፣ የማጋለጥ እና የፍርድ ሂደት በኩል፣ በመስቀሉ ማቆም እና ማስወገድ በኩል፣ በደሙ ማንጻት እና ማጠብ በኩል እና በመንፈስ መፍሰስ እና ፈጽሞ ሰርጾ ማርካት በኩል መንጻት እንችላለን—መዝ. 139፡23-24፤ 51፡7፣ 10፤ ራእ. 22፡1።
2. በእግዚአብሔር ንጹሕ ቃል ውስጥ ባለው የሕይወት ውኃ የማጠብ ሂደት በኩል መንጻት እንችላለን፤ አንድ ሰው ይበልጥ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በሆነ መጠን ይበልጥ ንጹሕ ይሆናል—መዝ. 12፡6፣ 119፡9፣ 140፤ ኤፌ. 5፡26፤ ኢሳ. 55፡8-11።
3. ዘሌዋውያን 19፡19 እግዚአብሔር እያንዳንዱ ነገር ያለምንም ድብልቅ እንደ ወገኑ እንዲሆን እንደሚፈልግ ይገልጣል—ራእ. 17፡3-6፤ ዘዳ. 22፡5፣ 9-11፤ ተዛ. ዘፍ. 1፡11፣ 21፣ 24-26፤ 2፡7-9፡-

ሀ. ከብቶችን ያለ ድብልቅ ማራባት ሕይወት እንዲደባለቅ እንደማይፈቀድ ያመለክታል፤ በእግዚአብሔር ሕይወት የሚኖሩ በሥጋ መኖር የለባቸውም—ተዛ. ገላ. 5፡16።

ለ. ዘርን ያለ ድብልቅ መዝራት በቃሉ አገልግሎት ውስጥ አንድ አይነት ዘር፣ አንድ አይነት ትምህርት ብቻ መዘራት እንዳለበት ያመለክታል—ልዩና ብቸኛው የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ትምህርት—ዘዳ. 22፡9፤ 1 ጢሞ. 1፡3-4፤ 6፡3።

ሐ. ግብአቶችን ሳይደባልቁ ልብስን መሥራት ምልልሳችን እንዲደባለቅ እንደማይፈቀድ ያመለክታል፤ በአዲስ ኪዳን ሕይወት እየኖሩ ያሉት በብሉይ ኪዳን ድንጋጌዎች መኖር የለባቸውም (ገላ. 2፡19-20፤ 5፡1-6)፣ የጌታ የሆኑትም በአሕዛብ ልማድ መሠረት መኖር የለባቸውም (ዘሌ. 20፡23፤ 18፡3፤ ተዛ. ኤፌ. 4፡17፤ ሮሜ 12፡2)።

4. አንደኛ ጴጥሮስ 1፡22 "ለእውነት እየታዘዛችሁ ግብዝነት ለሌለበት ለወንድማማች መዋደድ ነፍሳችሁን አንጽታችሁ እርስ በርሳችሁ ከልባችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ" ይላል፡-

ሀ. ይህ ማለት ነፍሳችንን (አእምሮአችን፣ ስሜታችንን እና ፈቃዳችንን) ማንጻት ከእግዚአብሔር ውጪ ካሉ ነገሮች ሁሉ ነጻ ማውጣት እና እንደ ብቸኛው ትኩረት እና ልዩና ብቸኛ ግብ እግዚአብሔር ላይ ማተኮር ነው (1 ቆሮ. 2፡9-10፤ 2 ተሰ. 3፡5)፤ በክርስቶስ ያለን እምነት (2 ጢሞ. 4፡7፤ ቲቶ 1፡1) ይዘት እና እውነታ የሆነውን እውነትን ስንታዘዝ፣ መላው ነፍሳችን በእግዚአብሔር ላይ ታተኩራለች፣ ከዚህም የተነሣ ከእግዚአብሔር ውጪ ካሉ ነገሮች ሁሉ ትነጻለች።

ለ. የነፍሳችን መንጻት እግዚአብሔርን በሙሉ ልባችን፣ በሙሉ ነፍሳችን፣ እና በሙሉ ኃሳባችን እንወደው ዘንድ (ማር. 12፡30) መላው ማንነታችን በእግዚአብሔር ላይ እንዲያተኩር ስለሚያደርግ፣ እንዲህ ያለው መንጻት ግብዝነት የሌለበትን የወንድማማች መዋደድ፣ እግዚአብሔር የወደዳቸውን ከልባችን አጥብቀን መውደዳችንን ያመጣል (ዮሐ. 13፡5፣ 14-17፣ 34-35፤ 2 ጴጥ. 1፡5፣ 7፤ ሮሜ 12፡9-11፤ 2 ጢሞ. 1፡6-7፤ 1 ተሰ. 3፡12፤ 4፡9-10፤ ዕብ. 13፡1፤ 1 ዮሐ. 2፡5-8፤ 3፡11፣ 23፤ 4፡7-8፣ 16-21)።

ለ. ለእግዚአብሔር ምስክር፣ ብዙዎች ለተካተቱበት መገለጡ ሌሎችን በእውነት ለማስተማር እኛ የተማርን መሆን ያስፈልገናል—2 ጢሞ. 2፡2፤ 1 ጢሞ. 3፡15-16፤ 6፡3፤ 1 ቆሮ. 14፡31፡-

1. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም በሐዋርያት ትምህርት፣ በጤናማው የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ትምህርት መሠረት እንደተገነባች በማመልከት፣ የቅድስቲቱ ከተማ፣ የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም አሥራ ሁለት መሠረቶች የአሥራ ሁለቱ የበጉ ሐዋርያት ስም አለባቸው—ራእ. 21፡14፤ ሐዋ. 2፡42፤ 2 ጢሞ. 1፡15፤ ቲቶ 1፡9፤ 2 ጢሞ. 2፡2።

2. ዕዝራ ከእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ጋር የሚገናኘውን የእግዚአብሔርን ሕግ በሚገባ የሚያውቅ ነበር፤ ሕጉ እንደ እግዚአብሔር ቃል፣ እንደ እግዚአብሔር ምስክር፣ እንደ እግዚአብሔር ማሳያ፣ እንደ እግዚአብሔር መገለጥ የክርስቶስ ምሳሌ ነው—ዘጸ. 16፡34፤ 34፡28፤ ተዛ. ራእ. 1፡2።

3. በተጻፈው ቃል ውስጥ እንዳለው እንደ ሕያዉ ቃል ወደ ክርስቶስ በመምጣት፣ የኢየሱስ ምስክር ለመሆን በእርሱ ለመሰረጽ እርሱ የሚተገበረው ቃል ሊሆንልን ይችላል—ዮሐ. 1፡1፣ ራእ. 19፡13፤ ዮሐ. 5፡39-40፤ 6፡63፤ ራእ. 1፡2፣ 10-11።

4. በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ትምህርት ልዩና-ብቸኛ አገልግሎት ውስጥ በመቆየት፣ በሕይወት ብርሃን ለመሞላት የቃሉን ውስጠ-መሠረታዊ ትርጉም መረዳት እንችላለን—ነህ. 8፡8፣ 13፤ ማቴ. 4፡12-16፤ ዮሐ. 1፡4-5።

5. በአዲሱ ባህል፣ በአዲሱ ሰው የአምላክ-ሰው ባህል ውስጥ አዲሱን ቋንቋ፣ "የአይሁድን ቋንቋ" መጠቀምን መማር አለብን—ነህ. 13፡23-24።

ሐ. በጸጋ መልሶ-መቀናበር ያስፈልገናል፣ ይህም፣ በሂደት ያለፈው ሦስታንዱ አምላክ ሕይወት እና ሁሉ ነገራችን ሲሆንልን ነው—1 ጴጥ. 5፡10፤ 2 ቆሮ. 13፡14፤ ዕብ. 10፡29፡-

1. አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን ለማፍራት ጸጋ ምንጩ፣ ንጥረ-ነገሩና መንገዱ መሆኑን በማመልከት አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት የአዲስ ኪዳንን ጸጋ ይወክላሉ—ራእ. 21፡14።

2. በጸጋ ላይ ጸጋ መቀናበር፣ በጸጋ መድከም፣ ጸጋን ማደል እና የጸጋን ቃል ማገልገል ያስፈልገናል—ዮሐ. 1፡16፤ 1 ቆሮ. 15፡10፤ 1 ጴጥ. 4፡10፤ ሐዋ. 20፡32።

3. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም የምትገነባው እግዚአብሔርና ሰው ብዙዎች የተካተቱበት አካል እና የጋራ ማደሪያ ስፍራ ይሆኑ ዘንድ ሰውን በሕይወትና በባሕሪይ ተመላኪነቱን ሳይጨምር ከራሱ ጋር አንድ ለማድረግ እግዚአብሔር ራሱን ወደ ሰው ውስጥ በማቀናበሩ ነው—ራእ. 21፡2-3፣ 10-11፣ 18-22።

4. መሥራት ያለብን አንድ ሥራ ብቻ ነው፣ እርሱም የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ሥራ ነው፤ በሕይወታዊ ማዳኑ ዋና ደረጃዎች—በዳግም መወለድ፣ በመቀደስ፣ በመታደስ፣ በመለወጥ እና ወደ መክበር በመምሰል—በኩል የመረጣቸውን ለማሳለፍ ሲቀጥል ሳለ በውስጣችን እየሠራ ካለው እግዚአብሔር ጋር አንድ መሆን ያስፈልገናል።
5. በዚህ መንገድ አንድ ዓይነት ወደምንሆንበት ከፍተኛ ነጥብ እስከንደርስ ደረጃ በደረጃ ወደ ላይ እንወጣለን፤ ሥጋ እና ፍጥረታዊ ማንነት አይኖርም፤ ሁሉም በመንፈስ ይሆናሉ፣ ሁሉም የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ማንነቶች ይሆናሉ፤ ይህ የእግዚአብሔር ሥራ ከፍተኛው ነጥብ ነው፣ እኛም አብሮ-ሠራተኞቹ እንሆናለን—ዮሐ. 5፡17፤ ፊልጵ. 2፡13፤ ራእ. 4፡3፤ 21፡11፤ 1 ቆሮ. 3፡9፣ 12፤ 2 ቆሮ. 6፡1፤ 1 ተሰ. 3፡2።
6. “አካሉ እንዲሆን እንደ መለኮትና ስብዕና መዋሐድ የክርስቶስን ቅንብር ያገኘ ዘንድ እና እንደ ዘላለማዊ መገለጡና ለሚዋጀው እግዚአብሔርና ለተዋጀው ሰው እንደ የጋራ መኖሪያ የክርስቶስን አካል ያገኘ ዘንድ፣ በሂደት ያለፈውና የተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ በበጎ ደስታው መሠረትና በኢኮኖሚው ውስጥ ላለው ከፍተኛው ውጥን ራሱን ወደ መረጣቸው ሕዝቡ ውስጥ እና የመረጣቸውን ሕዝቡን ወደ ራሱ ውስጥ እየገነባ ነው። የዚህ ተዓምራዊ መዝገብ መዋቅር ከፍተኛው-የመጨረሻው-ምርጡ መጠናቀቅ ለዘላለም አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ትሆናለች”—ዊትነስ ሊ።

መ. ቅድስቲቱ ከተማ እንድንሆን ለቤተ ክርስቲያን ሕይወት ቅዱስ ኑሮን እንድንኖር በእግዚአብሔር ለመሞላት ለእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ መለየት ያስፈልገናል—ራእ. 21፡2፤ 2 ጴጥ. 1፡4፦

1. የአእምሮ መታደስ እና የሚያስከትለው ልውጠት በዓለም ንጥረ-ነገር ከተዘፈቀው አሮጌ ተፈጥሮአችንና ኑሮአችን ይለዩናል፣ ያድኑንማል—ራእ. 21፡12፤ ሮሜ 8፡5-6፤ 12፡2፣ 5-11፤ ኤፌ. 4፡23።
2. መንፈሳችን ውስጥ በመኖር እና ክርስቶስን እንደ ተሰወረው መና በመብላት የእግዚአብሔር ሕንጻ ለመሆን ዓለምን ድል መንሣት እንችላለን—1 ዮሐ. 5፡4፣ 18-19፣ 21፤ ራእ. 2፡12-17፤ ተዛ. ዮሐ. 14፡30።
3. ምኞትን፣ ማታለልንና የገንዘብን ፍቅር በሚያካትተው በቢዝነስ ወይም በንግድ ክፋት ከምትታወቀው ከጣዖት አምላኪዋ የባቢሎን ዓለም ሙሉ በሙሉ መለየት ያስፈልገናል፤ የክርስትና ሕይወታችን የገንዘብ ፍቅር የሌለበት መሆን አለበት፣ የክርስትና ሥራችን ደግሞ ገንዘብ ማግኛ ንግድ መሆን የለበትም—ዘካ. 5፡5-11፤ 1 ጢሞ. 3፡3፣ 8፤ 6፡5-10፤ ሐዋ. 11፡29-30፤ 20፡33-34፤ 2 ጢሞ. 3፡2-4፤ ዕብ. 13፡5፤ 2 ቆሮ. 2፡17፤ 12፡15፤ ተዛ. 2 ነገ. 5፡15-27፦
   ሀ. ሰይጣን ነጋዴ ነው፣ ኃሳቡ ደግሞ እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረበትን ዓላማ የሚጻረር በሆነው በንግድ መርሁ መሠረት ነው—ሕዝ. 28፡16፣ 18፤ ኢዮ. 1፡9፤ ተዛ. ፊልጵ. 3፡7-8፤ ዘፍ. 1፡26።
   ለ. በባቢሎን ከሚሸጠው ጭነት፣ የመጀመሪያው ዕቃ ወርቅ ነው፣ የመጨረሻው ደግሞ የሰዎች ነፍሳት ነው፤ *የሰዎች ነፍሳት* ለመቀጠር ራሳቸውን የሚሸጡ ሰዎችን ያመለክታል—ራእ. 18፡12-13፤ ተዛ. 2 ጴጥ. 2፡3፣ 15።
   ሐ. ይህ የምትመጣዋን ባቢሎንን ብቻ ሳይሆን የዛሬውንም ዓለም ያሳያል፤ ሰዎች እግዚአብሔርንና ዘላለማዊ ዕጣ ፈንታቸውን ቸል በማለት ነፍሳቸውን፣ ሕይወታቸውን ማለትም ራሳቸውን ለሥራቸው ይሸጣሉ—ተዛ. ሉቃ. 12፡13-21።
   መ. የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት የእስራኤል ሕዝብ በምርኮኝነታቸው ጊዜ ከባቢሎናውያን የተማሩትን በንግድ ውስጥ ያለውን ክፋት ወደ ባቢሎን (ወደ ሰናዖር ምድር) እንዲመለስ ያደርጋል—ዘካ. 5፡10-11፤ ዘፍ. 11፡2፣ 9።

ሠ. ቤተ ክርስቲያንን እንደ እግዚአብሔር ቤት ለመጠበቅ ቅጥሩን መሥራት ያስፈልገናል፦

1. ንስሐ በመግባታችን፣ ኃጢአቶቻችንን በመናዘዛችን እና እንዲያነጻን እግዚአብሔርን በመጠየቃችን አማካኝነት በሚተገበርብን ድል በሚነሣው በበጉ ደም ቅጥሩን መሥራት እንችላለን—ራእ. 12፡11፤ መዝ. 51፡18።
2. የእግዚአብሔር መንጋ በክርስቶስ ሙሉ ሰው ይሆኑ ዘንድ የአዲስ ኪዳንን ልዩና ብቸኛ አገልግሎት አንዱን መለከት በመንፋት፣ ከጌታ የሚጠብቅ ማስጠንቀቂያ ጋር እና ከጌታ ጤናማ ትምህርት ጋር የእግዚአብሔርን ቃል ለማጠናቀቅ የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ በማወጅ የእግዚአብሔርን መንጋ በእረኝነት መንከባከብ አለብን—1 ቆሮ. 14፡8፤ ኤፌ. 4፡11፤ ሐዋ. 20፡26-35፤ ሕዝ. 33፡1-11፤ 34፡25፤ ቆላ. 1፡24-29።
3. ውጊያውን በአካሉ በመዋጋት ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅ ቅጥሩን መሥራት አለብን—ሮሜ 16፡20፦
   ሀ. አካሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ይለብሳል፣ ለእያንዳንዱ ብልትም ጥበቃ ይሰጣል፤ የአካሉን ጥበቃና ከለላ ለመቀበል የአካሉን ምክርና ጥበቃ መፈለግ አለብን—ኤፌ. 6፡10-20፤ ማቴ. 16፡18፤ ሐዋ. 21፡4፣ 11-12።
   ለ. መንፈሳዊ ውጊያ በዚህ መርህ መሠረት ነው—አንዱ ሺህ ያሳድዳል፣ ሁለቱ አሥር ሺህ ያሸሻሉ—ዘዳ. 32፡30፤ መክ. 4፡9-12፤ ዘጸ. 17፡11-13።

4. በምድር ላይ የእግዚአብሔርን መለኮትነት ብልጥግናዎች ፍላጎትን እና በመጠናቀቁ የደረሰበትን ሁሉ ለመጠበቅ ቅጥሩን መሥራት አለብን—ተዛ. ዮሐ. 1፡12-13፤ ኢሳ. 9፡6፤ 1 ቆሮ. 15፡45፤ 2 ቆሮ. 3፡17፤ 4፡5፤ ቆላ. 1፡18፤ ሐዋ. 2፡36፤ 5፡31፤ ዕብ. 4፡14፤ 9፡15፤ 7፡22፤ 8፡2፤ 1 ዮሐ. 2፡1፤ ዮሐ. 15፡26፤ ሮሜ 8፡34፣ 26።

ረ. ቤተ ክርስቲያንን እንደ እግዚአብሔር መገለጥ መገንባት እንችል ዘንድ በክርስቶስ በመኖርና ክርስቶስን በመኖር ክርስቶስን ማጉላት ያስፈልገናል—ዘጸ. 40፡34-35፤ 1 ነገ. 8፡1-11፤ ሮሜ 13፡14፣ 12፤ 1 ቆሮ. 3፡16-17፤ ፊልጵ. 1፡19-21፤ ራእ. 21፡3፣ 22፣ 10-11፡-

1. የከተማይቱ ቅጥር ለእግዚአብሔር መገለጥ ነው፤ ስለዚህ "ቅጥሩን መሥራት" (ነህ. 2፡17) ቤተ ክርስቲያንን እንደ እግዚአብሔር መገለጥ መገንባት ነው (ማቴ. 16፡18፤ ኤፌ. 2፡20-22፤ 4፡11-16፤ 1 ቆሮ. 3፡9-17፤ ራእ. 4፡3፤ 21፡11፣ 18-19)።
2. ዛሬ በምለሳው ጌታ እንደ መገለጡ በተገቢዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን የክርስቶስን ጤናማ ሁኔታ ለማደስ እየሠራ ነው—ኤፌ. 3፡16-21፤ ራእ. 4፡3፤ 21፡11፣ 18-19።
3. እግዚአብሔርን ለመግለጥ፣ በመላው የክርስቶስ አካል የመገጣጠም ሕይወት ውስጥ ከመለኮታዊው ሥላሴ ጋር የተዋሐደ ኑሮን በመኖር ከተፈጥሮአዊ ባሕሪያችን እና ራስን ከመምሰል መዳን ያስፈልገናል—ሮሜ 5፡10፤ ዘሌ. 2፡4-5፤ 1 ቆሮ. 12፡24-25።
4. እግዚአብሔርን ለመግለጥ ለክርስቶስ፣ ለሙሽራችን፣ እንደ ንጽሕት፣ ክብርት፣ እግዚአብሔርን የምትገልጥ ሙሽራ እንቀርብ ዘንድ በቃሉ ውኃ በመታጠብ በየዕለቱ መቀደስና መታደስ ያስፈልገናል—ቁ. 24፤ ኤፌ. 5፡26-27።

*© 2022 Living Stream Ministry*